የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በጎኸው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።


# እስከመቼ


መጋቢት ፯ እስከ መጋቢት ፲፫ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
March 7 to March 13, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፱
Volume I Number 9


## ኢትዮጵያዊያን ነን እናም እንኮራለን።

ኢትዮጵያዊነት የማንነትና የምንነት መገለጫችንና መግለጫችን ነው። ማንኛችንም የምንወለድበትን የመረጥን የለንም። የትም ተወለድን የትም፤ ያ ቦታ የማንነታችን፣ የታሪካችንና፣ የወደፊታችን ወሳኝና ተናጋሪ ነው። በዚች **እስከመቼ** ቁጥር ፱ ኢትዮጵያዊነት ለኛ ያለውን ትርጉም፣ ኢትዮጵያዊነት ለኛ የሚሰጠንን ሙቀት፣ ኢትዮጵያዊነት ለኛ ያሸከመንን ኃላፊነት በኩራት እንዘክራለን።

"ምንም ቢከፋ ዘመድ፤ ምንም ቢጠም መንገድ"፤ ይላሉ የራሳችን ለመቀበል አንገታችን ቀና ማድረግ እንዳለብን ሲነግሩን። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነታችን ለኛ ከዚያ በላይ ነው። ለወንዙ እንግዳ ላገሩ ባዳ ለማንነቱ የለው ፍዳ፤ ካልሆንን በስተቀር፤ በብዙ በኩል ልንኮራበት የሚገባ ኢትዮጵያዊነት አለን። በጣም ረዥም ተከታታይና አኩሪ ታሪክ አለን። በአሁኑ ሰዓት ደግሞ፤ ብዙ የወጣት ኃይል፣ አጥጋቢ የተፈጥሮ ሀብት፣ ከሁሉም የጎላ ደግሞ ታታሪ ሠራተኛ ወገን አለን። እኛ ሀገራችን ብለን ተቀበልነው አልተቀበልነው "እየተፈጨ እየተቦካ እየተሞተ እየተተካ" ሀገር ሀገር ሆኖ ሀገርነቱን ይቀጥላል።

ያለፈውን ታሪካችንን በሚመለከት ያለብን ኃላፊነት ግልፅ ነው። በደንብ ጠንቅቆ ማጥናት፣ ከጥንካሬውም ይሁን ከጉድለቱ ትምህርት መውሰድና ለነገዎቹ ማስተላለፍ ነው። የትናንት እስረኛ ሆነን አንገታችንን አንደፋም። እኛ በኛችን ያለው የዛሬ ባለቤትነትና የነገ ኃላፊነት ነው። ትናንት ለትናንት ተኑሯል። ዛሬ ለትናንት አይኖርም። የነገዎቹ ለዛሬ እንጂ ለትናንት ተጠያቂ አድርገው አይዙንም። የዛሬ ባለቤት ነን።

ሃቁን እናጢን። ኢትዮጵያዊያን ሀገራችንን በጣም እንወለን። ታሪክም፤ ካልደረሱብን ከማንም የማንደርስ፣ ካልነኩን እጃችንን የማናነሳ፣ ተፈታታኝ ሲመጣ አንድነታችን ከብረት የጠነከረ መሆኑን ነው የሚመሰክረው። በሀገር ውስጥ ለሥልጣን ሽሚያ የተደረጉ የርስ በርስ መፈናከቶች መታየት ያለባቸው፤ በተከሰቱበት የታሪክ ወቅትና በተገበሩበት ቦታ ነው። ከዚያ ውጭ አንጠልጥሎ ማየት የታሪክን ታሪክነት አለመገንዘብ ነው። ይህ ማለት ግን የኢሕአዴግ ሠራዊት የዋሁን የአኝዋክ ተወላጅ የጨፈጨፈው የዛሬው ዕልቂት ነገ የሀገር የውስጥ መፈናከት ተብሎ ይታያል ማለት አይደለም። በአኝዋክ ወገናችን የተፈፀመው ግፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ መታየት ያለበት ፍትህ ጠባቂ ክስተት ነው። ይኼን ለምሳሌ ጠቀስን እንጂ፤ ኢሕአዴግ የሚጠየቅባቸው ከዚህ የከፋና ያልከፋ ብዙ ክሶች አሉ። የዚች **እስከመቼ** ተልዕኮ ስላልሆነ ይኼን ለሌላ ጊዜ እናስተላልፈዋለን።

**ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!** የሀገርዎትን ታሪክ፣ በኢትዮጵያዊነትዎ የውስጥዎን ክብር፣ በኢትዮጵያዊነትዎ የሚሰማዎን ኃላፊነት **እስከመቼ** ለርስዎ ለማስረዳት አይዳዳትም። ሆኖም "ባለቤቱ ያቃለለውን አሞሌ ባለዳው አይቀበለውም" እንዲሉ፤ ይህ ኢትዮጵያዊነት በአንድ የተወሠነ የታሪክ ወቅት ወይንም በአንድ የተመቼው ባለሥልጣን እንዳሻው የሚተረጎም አለመሆኑን ለማሥመር ነው።

**ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!** በማንነትዎ ይኩሩ፤ ከማንም የሚወዳደር አኩሪ ሀገር አለዎ። አንገትዎን ያቅኑ። ዛሬ ታሪክ የጣለለዎትን ኃላፊነት በመወጣት፤ የነገዎች መኩሪያ ይሁኑ።

**ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ! እስከመቼ** ወደ ፊት የሚመለከት የፖለቲካ ፍልስፍና እንዲከተሉ ጥሪ ታቀርብልዎታለች። ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ይታገሉ። ከድርጅትና ከግለሰብ ጥቅም በፊት ሀገርን ያስቀድሙ። ይህ ነው ታሪካዊ ኃላፊነትን መወጣት። ይቺ ሀገራችን እርስዎና እኛ ነን ያለናት። ይንቁ! ይቁሙ! ይቆጠሩ!


**የእስከመቼ ዕትም የዝግጅት ቦርድ፤**
ድረስ ነጋ፣ ሕሊና ነጋሣና፣ ሀገሬ ተመቼ

eske.meche@yahoo.com